## በፌስ-ቡክ መድረካችን ላይ
## በሐምሌ ወር፥ ፳፻፰ ዓ. ም. ለቀረቡ ጥያቄዎችና ትችቶች፡
## ከኢእመ የተሰጡ መልሶች። ፩ኛ።

### ፩ኛ፤ ከቴዎድሮስ ኹናቸው፡- የመልስ ትች፡-

እግዚአብሔር የተመስገነ ነው። በመጀመሪያ እንዲህ ለመነጋገር ለመዎያየት ያበቃን እርሱ ነው። ምስጋና ገንዘቡ ነውና።

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አምናለው። በእግዚአብሔር አንድነት እና ሦስትነትም አምናለው። አብ ማለት አባት ነው። ወልድ ማለት ውሉድ( የተዎለደ)። መንፈስ ቅዱስ በሁሉ ቦታ ያለ የሚኖር የሚፀልል የሚያድር ቅዱስ መንፈስ ነው።

አባት ማለት ባል ነው ለሚለው እና እናት ማለት ሚስት ነው ለሚለው እኔንን አያስማማኝም።

ትዳር ቅዱስ ነው አዎ ቅ�ዱስ ነው ስጋዊ ቅ�ድስና ነው። ባልነትም ሚስትነትም ቅድስና ነው። ፍትዎትም ቅድስና ነው ስጋዊ ቅ�ድስና። ግን ቅዱስ የሚሆኑ በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ነው። ቅዱስ ብቻ ነው ሁሉን ቅዱስ የሚያረገው። ያለርሱ ቅድስና የለምና። ምክኒያቱም እግዚአብሔር የሌለው ሁሉ እርኩስ ነው።

እኔና የኔዎቹ ለተባለው በዚህ እናምናለን የኦርቶዶክስ ተዋህዶም ክርስትናም በዚህ አስተምህሮ ነው የምትመራው። እኔ በፍፁም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትናን ልዎክል አልችልም በፈፁም ግን እንደ አንድ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኝ ነኝ። አስተምህሮዋን የመረዳት የማዎቅ ሀላፊነት የሚጠብቅብኝን ማዎቅ ነው።

ስ[ሥ]ጋዊ ቅድስና እና መንፈሳዊ ቅድስና ይለያያል። የፍጡር ቅድስና እና የፈጣሪ ቅድስናም ይለያያል ፈፅሞ አንድ ሊሆኑ አይችሉም። እግዚአብሔር የአዳም አባት ይባላል እንጂ ባል አይባል[ም]። እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የጌታችን የመዳህ[ድኃ]ኒታችን የእየሱስ ክርስቶስ እናት ትባላለች እንጂ ሚስት አትባልም።

ታድያ ይህ የናንተ አስተምህሮ ከዎዴት የመጣ ነው?

ያባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር የተመሰገነ ነው ክብር ምስጋና ለርሱ ይሁን አሜን።

### ፪ኛ፤ ከቴዎድሮስ ኹናቸው፡- የነቀፋና የዘለፋ ትች፡-

አቤት ያዞ እንባ!!! በማር የተለወሰ መርዝ፤ ምን አለ እንዲህ ባትመፃደቅብን?

## ፫ኛ፤ ከቴዎድሮስ ኹናቸው፦ የስድብና የክስ ትችና አስተያየት፦

በጣም የሚገርም ነው ሌላው የሀሰት እና የምንፍቅና አስተምህሮህን ተወው እና ጥቂቱን በማየት ብቻ ላንትና አስተምህሮህ መልስ መስጠት በጣም ቀላል ነው።

፩. እግዚአብሔር አብ ማለት አባት ነው ካልክ በኋላ፡ በባልነት ትፈርጃለህ፤ አባት ፈጽሞ ባል ሊሆን አይችልም።

፪. እግዚአብሔር እም ትላለህ፤ ይህን ካንተ ነው የሰማውት።

፫. እም ወይም እናት፡ በምንም አስተሳስብ ሚስት የሚለውን ትርጉም አይሰጥም።

## ከኢእመ፡ ለሦስቱም የቀረቡ ጽሑፎች፡ በአንድነት የተሰጠ መልስ፦

ይድረስ፦ ለአቶ ቴዎድሮስ ኹናቸው!

በቅድሚያ፡ በእግዚአብሔር ስም፡ ኢትዮጵያዊ ሰላምታችንን እናቀርብልዎታለን።

የዘለፋና የነቀፋ፥ የስድብና የክህደት ቃሎችን አሳዝለው፡ በፌስ-ቡክ የይፋ መድረካችን ላይ፡ አከታትለው ላሠፈሩልን አጫጭር የጽሑፍ አስተያየትዎና ጥያቄዎችዎ፥ ትችትዎና ክስዎ፡ እግዜር ይስጥልን!

ለእነዚሁ አስተያየቶችዎና ጥያቄዎችዎ፥ ትችትዎና ክስዎ፡ መልሳችን አድርገን የሰጠነውን፡ ከዚህ የሚቀጥለውን ማብራሪያችንን ይመለከቱት ዘንድ የምናበረክትዎ፡ በደስታ ነው።

፩ኛ፡ *"እግዚአብሔር እም ትላለህ፤ ይህን ካንተ ነው የሰማውት።"* ላሉት፡ የእኛም መልሳችን፡ አጭርና ቀጥታ፥ ግልጽና እሙን ነው። ያም፡ "የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መሪዎች ከኾኑት፡ <u>ከኢትዮጵያ [ከእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም] እና ከኢትዮጵያዊው ልጇ [ከአማናዊው መልከ-ጼዴቅ፡ኢየሱስ መሲሕ] ብቻ ካልኾነ በቀር</u>፡ እንዲህ ያለውን መለኮታዊ እውነትና ረቂቅ ምሥጢር፥ ጥንታዊ ቍም-ነገርና አዲስ ትንግርት፡ ጥንትም፥ ዛሬም፥ ወደፊትም፤ ምንጊዜም ቢኾን፡ ታዲያ! ከሌላ፡ ከማንና ከየት ሊያገኙት አስበው ኖርዋል?" የሚለው ነው።

የእነርሱ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው፡ ነቢያት ኾነው፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ወደፍጥረተ-ዓለሙ የተላኩት ልኡካን ልጆቻቸውን፡ እነኄኖክንና ኖኅን፥ ኢትዮጲሱን ቀዳማዊ መልከ-ጼዴቅን፥ የአብርሃሙን ማእከላዊ መልከ-ጼዴቅን፥ የሙሴውን ካህን ዮቶርን፥ ለኢትዮጵያዊነት የበቁትን፡ ራሱን ሙሴንና የኢትዮጵያዊት ቤትሳባን ባል፡ ንጉሥ ዳዊትን፥ እንዲሁም ሰሎሞናዊቷን የምኒልክን እናት፡ ንግሥት ማክዳን የመሰሉት ቅዱሳንና ቅዱሳት ኹሉ፡ በእነርሱ ዕቅፍ ውስጥ ያሉ ናቸው።

፪ኛ፡ *"ታድያ ይህ የናንተ አስተምህሮ ከዎዴት የመጣ ነው?"* ሲሉ ለሠነዘሩት ጥያቄ፡ መልሳችን ይኸውልዎ፡-

ይህ የእኛ አስተምህሮ የመጣው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ከምትመራበትና በቀጥታ፡ ከፈጣሪዋ ከእግዚአብሔር ከተቀበለችው፥ በዘንድሮው ዘመን፡ ለ፯ሺ፭፻፰ (ሰባት ሺህ አምስት መቶ ስምንት) ዓመታት ባለጸግነቷ የበቃው ዕድሜዋ ጋር እንዳለ ኾኖ፡ እንደመምህራችን ኢየሱስ መሲሕ ቃል፡ ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ኢትዮጵያ ከኾነው፡ ከኦሪታውያኑ የአይሁድ ሊቃናትና ከኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን መነኮሳት እርሾ [አስተምህሮ]፡ ፍጹም ከነጻው፥ ከግእዛዊው የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖቷ ነው።

እርሱንም፡ ከአራቱ የሃይማኖትና የቃል-ኪዳን፥ የእግዚአብሔር ምስጋናና የድንግል ማርያም ሰላምታ ጸሎቶቻችን ውስጥ ተካትቶ ያገኙታል።

፫ኛ፡ በዚህ ሃይማኖታችን መሠረት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ የእግዚአብሔር ከኾነው በቀር፡ ሌላ ዓይነት ቅድስና ፈጽሞ የለም፤ ያም፡ አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም፡ የእግዚአብሔር የኾነው ብቻ ነው። በዚህ ረገድ፡ ተባዕቱ [ወንዱ]፡ "**ቅዱስ**"፥ እንስቲቱ፡ [ሴቲቱ]፡ "**ቅድስት**"፡ ይባላሉ። የቃሉ ትርጉም፡ "**ለእግዚአብሔር ብቻ፡ ተለይቶና ቀርቦ መሰጠት!**" ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ፡ "**ቅድስና**" ባለበት ዘንድ፡ በዚያ የሚኖረው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።

እርስዎ፡ ሌላ ዓይነት *ቅድስና* ያለ ይመስል፡ *"ስ[ሥ]ጋዊ ቅድስና እና መንፈሳዊ ቅድስና ይለያያል። የፍጡር ቅድስና እና የፈጣሪ ቅድስናም ይለያያል፤ ፈፅ[ጽ]ሞ አንድ ሊሆ[ኾ]ኑ አይችሉም።"* እያሉ፣ በቃሉም መካከል፡ የጥያቄ ምልክት እየሻጡ የጨመሩት፡ ከየት አምጥተው ነው? ይኼ፡ የባዕድ አምልኮ አስተምህሮና ይትበሃል ነው፤ ያም፡ ቀድሞ፡ የኦሪታውያኑ አይሁድ ካህናት፥ ኋላም፡ የኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን መነኮሳት፡ ወደኢትዮጵያ አምጥተው የዶሉት ነው።

ታዲያ! እርስዎና እርስዎን የመሰሉት፡ እየራሳችሁን፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ካላችሁ፡ ኢትዮጵያዊዉንና ቀዳሚዉን፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት ልትከተሉ ይገባችኋል እንጂ፡ ያልነበረውንና የሌለውን፡ የባዕዳኑን ይትበሃል፡ በዕውርነት ተቀብላችሁ፡ እንዴት እየራሳችሁን፡ ለዚያ ስሕተት ታስገዛላችሁ?! አይኾንም። አለዚያ፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት ኹሉ፡ ድንግል ማርያም የኾነችው፡ የእርሷ፡ "የኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም!" ተብላችሁ፡ በመለኮታዊው ቃል ልትካዱና ወደውጭ ልትጣሉ ነውና፡ በእውነተኛ ንስሓችሁ፡ ፈጥናችሁ፡ ወደልጅነታችሁና ወደነጋሢነታችሁ፥ ወደክህነታችሁም ተመለሱ!

፬ኛ፡ በውኑ፡ የተነሣንበትን ዓላማ በሚመለከት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በእርስዎና እርስዎን በመሰሉ ሰዎች ዘንድ ያለው፡ አሰልቺና የማያቋርጥ ችግር፡ ምን እንደኾነ ሊገነዘቡ ይፈልጋሉ? ይኼውልዎ፡-

እኛ፡ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አማካይነት፡ ከአያሌ ሺህ ዘመናት በፊት፡ ከእግዚአብሔር ያገኘነው አስተምህሮ፡ ምን ዓይነት እንደኾነ ለመገንዘብ፥ ጥረት ለማድረግም፡ በእውነት አለመፈለጋችሁ ነው። አኹን፡ ይህን አስተምህሮ፡ እንደገና ለመረዳት፡ በእውነት ከፈለጋችሁ፡ እስኪ፡ ባጭሩ፡ የሚከተለውን ይመልከቱ፦

እግዚአብሔር፡ ጥንት በሌለው ዘመን፡ ገና፡ ጾታ-ባልነበረው፡ አንድ አምላክነት፡ በራሱ ህልው ኾኖ ሲኖር ሣለ፡ ዓለማትን፡ ዛሬ ባሉበት መልክና ይዘት ለመፍጠር አሰበ። ከመፍጠሩ በፊት ግን፡ ያደረገውን፡ ይህን መለኮታዊ ዕፁብ ድንቅ ምሥጢር ይከታተሉ፤ የመጀመሪያው ሥራው፡ ይኸውልዎ፦

ሀ) ጾታ-አልባ የኾነ፡ አንድ ራሱን፡ እኩል፡ ለኹለት ከፈለ፤

ለ) አንድ ወገኑ፡ "እግዚአብሔር አብ" ኾነ፤

ሐ) ጾታውም፡ በወንድነት ተለየ፤

መ) "ድንግሉ ሙሽራ፡ [ባል]" ተባለ።

ሠ) አንዲቱ ወገኑም፡ "እግዚአብሔር እም" ኾነች፤

ረ) ጾታዋ፡ በሴትነት ተለየ፤

ሰ) "ድንግሊቷ ሙሽሪት፡ [ሚስት]" ተባለች።

ሸ) ከዚህ የተነሣ፡ እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር እም፡ አንዱን፥ ወንዱን ጃንደረባ ልጃቸውን፡ እግዚአብሔር ወልድን ወለዱ፤

ቀ) እንደዚሁ ኹሉ፡ እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር እም፡ አንዱን፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሳቸውን በጾታ-አልባነት አሠረፁ።

በ) ስለዚህ፡ እግዚአብሔር አብ፡ የእግዚአብሔር ወልድ አባት፣ እግዚአብሔር እም፡ የእግዚአብሔር ወልድ እናት ኾኑ።

ተ) እንደዚሁ ኹሉ፡ እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር እም፡ የአንዱ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አሥራጊ ኾኑ።

፫ኛ፡ ታዲያ! በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እና በልጆቿ ዘንድ፡ እውነታው፡ ይህ ኾኖ ሣለ፡ እርስዎ፡ በመጀመሪያው ትችትዎ፦ *"እግዚአብሔር የአዳም አባት ይባላል እንጂ ባል አይባል[ም]። እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የጌታችን የመዳህ[ድኃ]ኒታችን የእየሱስ ክርስቶስ እናት ትባላለች እንጂ ሚስት አትባልም።"*

በኋለኛው ትችትዎ ደግሞ፡ *"እግዚአብሔር አብ ማለት አባት ነው ካልክ በኋላ፡ በባልነት ትፈርጃለህ፤ አባት ፈፅሞ ባል ሊሆን አይችልም።*
*እም ወይም እናት በምንም አስተሳሰብ ሚስት የሚለውን ተርጉም አይሰጥም።"* ማለትዎን፡ የተዛባና የማይጣጣም እንጂ፡ ትክክለኛ አገላለጽ ኾኖ አላገኘነውም።

በእግዚአብሔር ዘንድና እኛም፡ ከእግዚአብሔር፡ ባገኘነው ሥርዓት፡ አባት፡ ለልጁ፡ "አባት"፥ እንዲሁም፡ እናት፡ ለልጇ፡ "እናት"፥ ደግሞም፡ባል፡ ለሚስቱ፡ "ባል"፥ ሚስትም፡ ለባሏ፡ "ሚስት" ይባላሉ እንጂ፡ እርስዎ ያሉት አገላለጽ የሚያስኬድ አይኾንም።

በቅድስና የጠራውንና የቀናውን፥ የበራውንና የሠመረውን፥ ያማረውንና የጣፈጠውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል፡ ለምን፡ እንዲህ ያድበሰብሱታል? ስለምንስ፡ ያማስኑታል? ይህን ያህልስ፡ ለምን ይፈሩታል? ራስዎ፡ እንዲህ ፈርተውት፡ ሌሎችንም ሊያስፈራሩበት የሚገባ አይደለም። በእግዚአብሔራዊው ሕጋዊ ጋብቻ፡ አባትነት እና እናትነት፡ ያለባልነት እና ያለሚስትነት፡ እውን ሊኾን ይችላልን? አይችልም፤ ከአባትነት እና ከእናትነት በፊት የሚቀድመው እኮ፡ ባልነት እና ሚስትነት ነው፤ አይደለምእንዴ? አዎን! በእርግጥ ነው።

ወይስ፡ እርስዎ፡ እግዚአብሔር የሠራውን፡ ቅዱሱን የጋብቻ ሥርዓት፡ ሰዎች፡ እየከፋፈሉ፥ ከዚያም ላይ፡ በእየዓይነቱ የፈለጉትን እየመራረጡ፡ "እኩሉን 'ቅዱስ'፥ ሌላውንም፡ 'ርኵስ' ብለው መመደብ ይችላሉ!" ማለትዎ ነውን? ይህ፡ አይቻልም። ወይስ፡ እንዳስለመዱት፡ እግዚአብሔር ያልሠራውን፡ "አርዑተ-ምንኵስናን"፡ "ቅዱስ" ብለው፡ ያን እግዚአብሔራዊዉን ዓይነት ቅድስና አቀዳጅተው፥ እግዚአብሔር ለሠራው፡ለሥርዓተ-ጋብቻ ግን፡ ተራውን ዓይነት፥ በቃሉም መካከል፡ የጥያቄ ምልክት እየሻጡ የጨመሩበትን ቅድስና ሊያከናንቡት ፈልገው ነው?

ለእርስዎ የሚጠቅምዎት፥ ለሕይወትዎም ደኅንነት ሲሉ፡ ራስዎን፡ በትሕትና አዋርደው፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት መከተሉ እንጂ፡ *"አባት ማለት ባል ነው ለሚለው እና እናት ማለት ሚስት ነው ለሚለው እኔንን አያስማማኝም።"* ማለትዎ አይደለም። ስለዚህ፡ ይህ አያስኬድዎትምና፡ አስበውበት፡ በንስሓ፡ ወደመንፈስ ቅዱስዋ ዕውቀት ይመለሱ!

እንኳንስ፡ እግዚአብሔር በሠራውና በመሠረተው፥ ራሱም በፈጸመውና ባስፈጸመው፡ በመለኮታዊው ሥርዓተ-ጋብቻ ውስጥ በተካተቱት፡ "ባል" እና "ሚስት" በተባሉት ቅዱሳት ቃላት ዘንድ ይቅርና፡ በሌሎቹም ተራ ቃላት ዘንድና በትርጉማቸው ረገድ ያለው፡ ጥቃቅኑ ስሕተት እንኳ ቢኾን፡ እንግዴህ ወዲህ፡ በዲያብሎስ የክፋት ኃይል፥ የኃጢአት ጠንቅና የሞት ፍላፃ መሣሪያነት፡ ለሙስና ወደተዳረጉበት፡ ወደዓመፃው መረንነት ተጥለው እንደወደቁ አይቀሩም፤ ያ፡ የጨለማ ዘመን አብቅቷል፤ አልፏል፤ ኹሉ፡ እንዲሁ ተትቶ፥ እንዲሁ ተጥሎ የሚቀር አይደለም። ስሕተቶቹን ቀፍቅፈውና ዐቅፈው ለሚገኙት፡ ለእነዚሁ፡ ለዲያብሎስ የክፋት ጥሪቶች፡ አንዳችም መሸሎኪያ ቀዳዳ፥ መሸሸጊያ ጓዳም፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እንዲኖራቸው ሊደረግ ከቶ የሚቻል አይኾም።

ዲያብሎስ፡ እስካኹን፡ በዚህ ረገድ፡ በሰዎች ላይ ሲያደርስና ሲያካኼድ፥ ሲፈጽምም የኖረው፥ አኹንም እያደረገ ያለው፡ ረቂቅ የጥቃት ዘመቻውና ውጊያው፡ ፍለጋውና ሰንኮፉ ሳይቀር፡ ኹሉም ዓይነት ጥፋት፡ከየተደበቀበት ሥርቻ እየተበረበረ የሚጋለጥበትና የሚከሠትበት፥ በዚያም ፋንታ፡ የእግዚአብሔር እውነት የምትተካበት፡ የመለኮታዊው ዐዋጅ ዘመን መግባቱን፡ እርስዎ አልሰሙም ይኾን? ካልሰሙት፡ ይኸው ይስሙት!

ቀኑ፡ እነሆ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምና የልጇ የወዳጇ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የኾነውን መለኮታዊ ትንግርቱን፡ በታላቅ ብርሃን፣ በገሃድና በይፋ የሚያሳይበት ስለኾነ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታቸው አማካይነት፡ ይኸው፡ ኹሉንም፡ በሚያስተካክለው፡ እያስተካከለው ነው፤ በሚያስወግደውም፡ እያስወገደው ነው።

"ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ! በሰማያትና በምድር፡ ፈጽሞ የመላ ነው!" የተባለው "እግዚአብሔር ጸባዖት! አሸናፊው እግዚአብሔር!" በፈጠረውና በባለቤትነት በያዘው ፍጥረተ-ዓለም ውስጥ፡ ዲያብሎስ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እስካኹንም ኾነ፥ አኹንና ወደፊትም ቢኾን፡ በረቂቁም ኾነ፡ በግዙፉ ፍጥረት ዘንድ፡ አንዲት ጋት ቀርቶ፣ አንዲት ዐጥቅ፡ የባለይዞታነት ሥፍራ፡ ጨርሶ የለውም፤ ይኸው እየተባረረና እየተሳሳደደ ነው። ስለዚህ፡ "አይሁድ ነን! ክርስቲያን ነን!" በሚሉ፡ በሰዎች ሰይጣናዊ አገዛዝና አሠራር፡ እንደእስከዛሬው ኹሉ፡ ዛሬም፡ "አሥራት በኵራት" እየተባለ፡ ከየቍሳቍሱና ከየምናምኑ ኹሉ ላይ እየተዋጣ፡ ለዲያብሎስ የሚቀርብለት የወግ ማዕርግ ድርሻ፡ አዎን! እንግዴህ ወዲህ፡ የለም። ኹሉም፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ ነው።

፫ኛ፡ እዚህ ላይ፡ ለዚህ ሓተታችን ብርቱ ምስክርነት ይረዳዎ እንደኾነ፡ ልንጠቅስልዎ የምንፈልገው፡ በሓዋርያት ዜና መዋዕል ውስጥ የተነገረውን፡ የሊቀ-ሓዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስንና የአረማዊዉን ሮማዊ፡ መቶ አለቃ ቆርነሌዎስን ዝክረ-ነገር ነው። ያ ዝክረ-ነገር፡ ለብዙዎች የዘመኑ ትውልድ አባሎች፡ እጅግ ጠቃሚ የኾነ ትምህርታዊ ማስረጃነት ያለው መልእክት ስለኾነ፡ ለእርስዎም፡ በምግባር ላይ ቢያውሉት እንደሚበጅዎ እናምናለን።

ያ ዝክረ-ነገር እንደሚያመለክተው፡ እግዚአብሔር፡ በዚያ መልእክቱ ሊያስተምር የተዘጋጀው፥ ያስተማረውም፡ በጴጥሮስና በሓዋርያት ዘንድ፡ በአረማዊነቱና በአሕዛብ ወገንነቱ የታወቀውን፡ ቆርነሌዎስን ሳይኾን፡ ከእርሱ ይልቅ፡ የሓዋርያት አለቃ የኾነውን፥ መንፈስ-ቅዱስም የወረደበትን ቅዱስ ጴጥሮስንና ወንድሞቹን ቅዱሳን ሓዋርያትን መኾኑን፡ የመጽሓፉ ክፍል በሚበቃ ያስረዳልና፡ እባክዎ፡ የሚያውቁትም ቢኾኑ እንኳ፡ እንደገና፡ በቅድሚያ ያንብቡት! (የሓዋ. ምዕ. ፲ እና ፲፩፥ ቍጥር ፩-፲፰።)

ይኸውም፡ በአንድ ወገን፡ በቂሣርያ ከተማ ይኖር የነበረው አረማዊው ቆርነሌዎስ፡ ሃይማኖቱ [ጸሎቱ] እና ምግባሩ [ምጽዋቱ]፡ ከእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ ፍሬያማነትን ያገኘለት መኾኑ፡ በቤቱ በተገለጠው፡ በእግዚአብሔር መልአክ የተበሠረተለት ሲኾን፥ ኋላም፡ ቅዱስ ጴጥሮስ፡ እዚሁ አረማዊ ቤት በገባ ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በአረማውያኑ ላይ ሲወርድባቸው፥ በመንፈስ ቅዱስም ሲጠመቁ፡ ራሱ [ቅዱስ ጴጥሮስ] የተመለከተ መኾኑ የታየበት መድረክ ነው።

በሌላው ወገን ደግሞ፡ "በበዓለ-ሃምሳ ዕለት፡ መንፈስ ቅዱስ የወረደባቸው በመኾኑ፡ በሃይማኖታቸውና በምግባራቸው ፈጽመው በቅተዋል!" የተባሉት፡ ሊቀ-ሐዋርያት ጴጥሮስና ወንድሞቹ ሐዋርያት፡ አንድ አይሁዳዊ፡ ሌላውን ሰው፡ '**ርኵስና የሚያጸይፍ ነው!**' ብሎ በማመን፡ ከዚያ ባዕድ ወገን ጋር እንዳይተባበር፥ ወይም፡ እንዳይቃረብ በሚያደርገው ኦሪታዊ ልማዳቸው፡ አኹንም ገና፡ ተተብትበውና ተቀፍደው በሚገኙበት ጊዜ፣ ይኸው ቅዱስ ጴጥሮስ፡ ወደቆርነሌዎስ ቤት ለመምጣት ከመነሣቱ በፊት፡ ገና በኢዮጴ ከተማ፡ በሰገነት ላይ ሣለ፡ ለቅዱስ ጴጥሮስ የታየውና ያ የእግዚአብሔር መልአክ፡ በዚሁ ሊቀ-ሐዋርያት ላይ የመሰከረበት፡ [የቅዱስ ጴጥሮስን] የሃይማኖቱን ጕድለትና የምግባሩን ስንኩልነት፡ ሌላው የመድረክ ማረጋገጫ ትርእይት መኾኑ ነው።

አዎን! መልአኩ፡ ሰማይ ተከፍቶ፡ ከዚያ በወረደ መጋረጃ ላይ፡ የሠፈሩትን፡ የምድር እንስሳትና የዱር-አራዊት፥ የሰማይ አዕዋፋትም፡ ለሊቀ-ሐዋርያት ጴጥሮስ እያሳየ፡ "**ኅርድ! ወብላዕ! ዐርደህ ብላ!**" ባለው ጊዜ፡ "**ሐሰ ሊተ እግዚኦ! ግሙራ ኢቦአ ርኩስ ውስተ አፉየ፤ ወኢበላዕኩ፡ ዘኢኮነ ንጹሐ።** አቤቱ! ሓሰት ይኹንብኝ! ርኩስ ነገር፡ ፈጽሞ፡ በአፌ ገብቶ አያውቅም። ንጹሕ ያልኾነም፡ በልቼ አላውቅም።" ብሎ ስለመለሰ፡ ያ ቃል፡ ደግሞ፥ እንደገናም፡ ሦስተኛ፡ "**ዘእግዚአብሔር አንጽሐ፡ አንተ ኢታስተራኵስ!** እግዚአብሔር አንጽቶ የፈጠረውን፡ አንተ አታርክስ!" ብሎት፡ ወደሰማይ ተመለሰ።

አዩ! ዲያብሎስ፥ ወይም፡ የሰው፡ የየራሱ ሰይጣናዊ አስተሳሰብ፡ እርስዎንና እርስዎን የመሰላችሁትን ብቻ ሳይኾን፡ ቅዱስ ጴጥሮስንና ሐዋርያትን ሳይቀር፡ እንዴት አድርጎ ሊያሳስት፣ ማሳሳት ብቻ ሳይኾን፡ ስሕተቱን እንደሃይማኖት ሊያሳምን እንደቻለ፡ እውነታውን ተመለከቱት አይደለምን? በዚህም ረገድ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በርኩስ መንፈስ ላይ፡ ድልን ባይቀዳጅ ኖሮ፡ እውነተኞች የእግዚአብሔር ሰዎች ኹሉ፡ ይኼኔ፡ ምን ይበጃቸው ነበር? ምንጊዜም፡ የፍጥረት ምስጋና፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ይኹን!

በአንድ በኩል፡ እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ አንጽቶና ባርኮ፥ ቀድሶም የሠራውን፥ የፈጸመውንም፡ የሥርዓተ-ጋብቻ አንዱ ዋና አካል የኾነውን ባልና ሚስትነትን፡ እርስዎ፡ "**ባል**"፥ "**ሚስት**" ከሚሉት፡ ከዝርዝር ቃሎቹ ጋር፡ እንደርኵስ በመቍጠር፡ እንዴት፡ ከእግዚአብሔር ቅድስና ሊያወጡት እንደሚሞክሩ፡ እያዩት አይደለምን? በሌላ በኩል ደግሞ፡ በእርስዎ ዘንድ፡ አርዑተ-ምንኵስናን፡ ከሥርዓተ-ጋብቻ ይልቅ፡ እጅግ ከፍ አድርገው በማሳየት፡ እንዴት፡ ለእግዚአብሔር ቅድስና እንዳበቁት አይመለከቱም?

እንግዴህ፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት፡ እውነተኞች የኢትዮጵያ ልጆች ከኾናችሁ፡ አዎን! እየራሳችሁን፡ እንደሊቀ-ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስና እንደቀሩት ሐዋርያት፡ በንስሓ መመለስና መስተካከል አለባችሁ።

፯ኛ፡ በማጠቃለያ፡ እርስዎ፡ *"በማር የተለወሰ መርዝ! ...ምን አለ እንዲህ ባትመፃደቅብን! ...አቤት ያዞ እንባ!!! ...ሌላው የሀሰት እና የምንፍቅና አስተምህሮህን ተወው!"* እያሉ በማከተተል የተቹትና የወቀሱት፥ የነቀፉትና ያስተሓቀሩት፥ የዘለፉትና የከሰሱት፡ ይህን ኢትዮጵያዊዉን የመንፈስ ቅዱስን የዕውቀት ጸጋ አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ።

እንግዲያ፡ የሰማዩ አባታችንና የሰማይዋ እናታችን ቅድስት ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም፡ በልጃቸው በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ ይህን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን የዕውቀት ጸጋ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ በኾነ ኢትዮጵያዊ ሰውነት አማካይነት፡ ለእርስዎና እርስዎን ለመሰሉት ኹሉ፡ እንዲህ አድርገው፡ ሲያቀርቡላችሁ፡ "አንቀበልም! እንዲያውም፡ እንቃወማለን!" ብላችሁ ከጸናችሁ፡ ከላይ፡ ቀደም ብለን፡ እንዳመለከትንዎ፡ ለራስዎ ሲሉ፡ በእውነተኛ ንስሓ ለመመለስ ፈቃደኛ ካልኾኑ በቀር፡ የሚጠብቅዎ ምን እንደኾነ አውቀውታል? ምናልባት፡ ካላወቁት፡ በዚህ ረገድ ያለው፡ የመለኮታዊው መምህራችን ቃል ይኸውልዎ፡-

**"በእንተዝ እብለክሙ፡- 'ኵሉ ኃጢኣት፥ ወፅርፈት፡ ይትኃደግ ለሰብእ፤ ወዘሰ፡ ፀረፈ ዲበ መንፈስ ቅዱስ፡ ኢይትኀደግ ሎቱ። ወዘሰ፡ ነበበ ቃለ፡ ላዕለ ወልደ-ዕጓለ-እመሕያው፡ ይትኃደግ ሎቱ፤ <u>ወዘሰ፡ ነበበ ላዕለ መንፈስ ቅዱስ፡ ኢይትኀደግ ሎቱ! ኢበዝ ዓለም፤ ወኢበዘይመጽእ።</u>**

"ስለዚህ እላችኋለሁ፡- 'ኃጢኣትና ስድብ ኹሉ፡ ለሰው፡ ይሰረይለታል [ይቅር ይባልለታል]፤ መንፈስ-ቅዱስን የሰደበ ግን አይሰረይለትም። በማርያም ልጅ ላይ፡ ቃልን የተናገረ፡ ይሰረይለታል፤ <u>በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የተናገረ፡ አይሰረይለትም! በዚህ ዓለም ቢኾን፤ በሚመጣውም ቢኾን።"</u> (ማቴ. ፲፪፥ ፴፩-፴፫።)